# ጉዳዮን ማረጋገጥ - ማስረጃና የፍርድ ቤት መጥሪያ

ይህ የመረጃ ወረቀት ጉዳዮን በፍርድ ቤት እንዴት ማረጋገጥ እንደሚችሉ ይገልፃል፡፡ ተጨማሪ ድጋፍ የሚፈልግ ተከራይ ወይ አከራይ ወደ ተከራይና አከራይ ምንጭ ማእከል ወይ ለሌላ ጠበቃ ማናገር ይችላል፡፡ ህጋዊ ድጋፍ የት እንደሚያገኙ በተመለከተ በዚህ ገፅ መጨረሻ ላይ መረጃ አለ፡፡

## ማስረጃ ምንድን ነው?

ማስረጃ ማለት የእርስዎን ወገን ጉዳይ ለማረጋገጥ የሚያግዝ ማንኛውም ነገር ሲሆን ምን እንደተፈጠረ ለዳኛው የሚነግሩትን ያካትታል፡፡ ፎቶዎች፣ ወረቀቶችና ሌሎች ነገሮችም እንደ ማስረጃ ጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡ ሂደቱ ለሁሉም ሰው ፍትሀዊ እንዲሆን፤ ዳኛው ሊጠቀሙበት ስለሚገባው ማስረጃ የሚወስኑበት ሕጎች አሉ፡፡ ሕጎቹ ውስብስብ ሊሆኑ ስለሚችሉ ጉዳዮን ለማረጋገጥ ስለሚጠቀሙባቸው ማስረጃዎች ዓይነት ከጠበቃዎ ጋር መነጋገር ይችላሉ፡፡

ለምሳሌ ጥገና መካሄዱን ወይ አለመካሄዱን ለማረጋገጥ አብዛኛው ግዜ ለዳኛው ፎቶ ማሳየትና በአይኖ ያዩትን መናገር ይችላሉ፡፡ ነገር ግን፣ ለዳኛው ፍርድ ቤት ውስጥ የሌለ ሰው የነገሮትን ነገር መናገር ወይ በፅሁፍ የፃፈውን ሰው ፅሁፍ ማሳየት አይችሉም፡፡

## የቤት ምርመራ ሪፖርትን እንደ ማስረጃ መጠቀም እችላለሁ?

አዎ፣ አብዛኛው ግዜ የቤት ውስጥ ምርመራ ሪፖርትን እንደ ማስረጃ መጠቀም ይችላሉ፣ ነገር ግን አብዛኛው ግዜ ከምርመራ ፅህፈት ቤት የመጣ ምስክር ፍርድ ቤት ውስጥ ያስፈልጋታል፡፡ የቤት ውስጥ ምርመራ ሰራተኛ ፍርድ ቤት እንዲመጡ ለማድረግ የፍርድ ቤት ማዘዣ መስጠት ይኖርቦታል፡፡ መርማሪው የቤት ውስጥ ምርመራ ድርጅቱ የምርመራ ውጤት በምን መልኩ እንደሚያስቀምጥ ማስረዳት ይኖርበታል፣ ምክንያቱም ዳኛው መረጃው ላይ እምነት እንዲኖረው፡፡

## የፍርድ ቤት ማዘዣ ምንድን ነው?

ጉዳዮ ወደ ፍርድ ቤት የሚሄድ ከሆነ፤ ስለእርስዎ መረጃ ላለው ሰው ወይ ድርጅት የፍርድ ቤት መጥሪያ መስጠት አለቦት፡፡ የፍርድ ቤት ማዘዣ ማለት ግለሰብ ወይ ድርጅት ከጉዳዮ ጋር የተያያዘ መረጃ ወይ ሌሎች የሚያዙ ነገሮች እንዲያቀርቡ ወይ እንዲመሰክሩ ወደ ፍርድ ቤት እንዲመጡ የሚያዝ ወረቀት ነው፡፡ የሆነ ሰው በጉዳዮ ላይ እንዲመሰክሩ ከፈለጉ፣ ነገር ግን ግለሰቡ ወደ ፍርድ ቤት መምጣታቸውን እርግጠኛ ካልሆኑ በዚህ ሰው ላይ የፍርድ ቤት ማዘዣ ማውጣት ይችላሉ፡፡ ለሆነ ግለሰብ ወይ ድርጅት የፍርድ ቤት ማዘዣ ከሰጡ በተባለው ግዜ ፍርድ ቤት መጥተው መመስከር ይኖርባቸዋል፡፡

ግለሰቡ ወይ ድርጅቱ እርስዎ ለጉዳዮ የሚፈልጉት መረጃ፣ ፎቶግራፍ፣ ወይ ሌላ መረጃ ካላቸው ለእርስዎ እንዲሰጡት የፍርድ ቤት ማዘዣ መስጠት ይችላሉ፡፡ ያ ግለሰብ ወይ ድርጅት ከፍርድ ሂደት ቀን በፊት ሊሰጥዎት ወይ የፍርድ ሂደት ቀን ወደ ፍርድ ቤት ማምጣት ይኖርባቸዋል፡፡

በዲሲ ውስጥ ወይ በዲሲ ዙርያ 25 ማይል ውስጥ ለሚገኝ ማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት የፍርድ ቤት ትእዛዝ መስጠት ይችላሉ፡፡

በፍርድ ቤት ትእዛዝ ላይ ስለ ጉዳዮ መረጃ መሙላት ይኖርቦታል፡፡ መረጃ ወይ ሌላ ማስረጃ እየጠየቁ ከሆነ የሚፈልጉትን ነገር መፃፍ ይኖርቦታል፡፡

## በጉዳየ ላይ ላሉት ሌላኛው ወገን የፍርድ ቤት መጥሪያ መስጠት እችላለሁ?

በጉዳዮ ላይ ላሉት ሌኛው ወገን የፍርድ ቤት መጥሪያ መስጠት አይችሉም፡፡ ከጉዳዮ ሌላኛው ወገን ተከራይ ወይ አከራይ መረጃ ከፈለጉ ይህን መረጃ ለማግኘት የፍርድ ቤት ትእዛዝ መጠቀም አይችሉም፡፡ በዚህ ፈንታ፣ ማድረግ ያለቦት ከአከራዮ መረጃ ለማግኘት የፅሁፍ ጥያቄ ማቅረብ አለቦት፡፡ ይህም ‹‹ግኝት›› ተብሎ ይጠራል

በጉዳዮ ላይ ግኝት ማካተት ከፈለጉ፣ ጠበቃዎን ማናገር አለቦት፡፡ አብዛኛው ግዜ ለሌላኛው ወገን አከራይ ወይ ተከራይ የግኝት ጥያቄ ለማቅረብ ፍርድ ቤት ሞሽን ማስገባት ይኖርቦታል፡፡ በጉዳዮ ላይ የጁሪ ትራየል ጥያቄ ካለ፤ ልዩ ፍቃድ ሳይጠይቁ ለሌላኛው ወገን የረወሰነ ግኝት ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ፡፡

## የፍርድ ቤት መጥሪያውን እንዴት እሰጣለሁ?

ጠበቃ ካልሆኑ የፍርድ ቤት መጥሪያውን ከፍርድ ቤት መጠየቅ አለቦት፡፡ የፍርድ ቤት መጥሪያው በተከራይና አከራይ ፍርድ ቤት ፀሀፊ መፈረም አለበት፡፡ የተከራይና አከራይ ፍርድ ቤት ፅህፈት ቤት (ክፍል 110) ነፃና ፊርማ ያለው የምስክር መጥሪያ ሊሰጦት ይችላሉ፡፡

መረጃ ለመጠየቅ ወይ ሌላ የሚያዝ ነገር ለመጠየቅ ብለው የፍርድ ቤት መጥሪያ እየሰጡ ከሆነ፤ በዚህ ጉዳይ ላይ ላሉት አካላት የመጥሪያውን ቅጂና ማስታወቅያ መስጠት አለቦት፡፡

በፍርድ ቤት መጥሪያው ላይ የሚፈልጉትን መረጃ ወይ የሚፈልጉትን ምስክር ከገለፁ በኋላ ስሙ ለተጠቀሰው ሰው ወይ ድርጅት የፍርድ ቤት መጥሪያው መሰጠት (መድረስ) አለበት፡፡ ቅጂ ሳይሆን ኦርጅናል የፍርድ ቤት መጥሪያ መሰጠት አለበት፡፡ የፍርድ ቤት መጥሪያውን

የሚሰጠውሰውዕድሜቢያንስ 18 መሆን አለበት እንዲሁም በጉዳዩ ላይ አካል መሆን የለባቸውም፡፡ በጉዳዩ ውስጥ ያሉት ተከራይ ወይም አከራይ የፍርድ ቤት መጥሪያ መስጠት አይችሉም፡፡

የፍርድ ቤት መጥሪያ ከተሰጠበኋላ የሰጠውሰውበፍርድ ቤት መጥሪያ ጀርባ ላይ ባሉት ቅጂዎች ‹‹መሰጠቱን ማረጋገጫ› መሙላት አለበት፡፡ ይህምየፍርድ ቤት ትእዛዝ የሰጠውሰውእንዴትና መቼ እንደሰጠ መረጃ ይሰጣል፡፡ ይህ የካርቦን ቅጂ ከሰጠውሰው ፊርማና ኦርጅናል ‹‹መሰጠቱን ማረጋገጫ› በማካተት በተከራይና አከራይ ፀሃፊ ፅህፈት ቤት መግባት አለበት፡፡ ሌላውን የካርቦን ቅጂ ለራስዎት ይያዙት፡፡

## ለፍርድ ቤት መጥሪያ ክፍያ አለው?

የፍርድ ቤት መጥሪያዎ የሆነ ሰውእንደ ምስክር ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ የሚጠየቅ ከሆነ ያንን ሰውየምስክር ክፍያ መክፈል አለቦት፡፡ አሁን ያለውየምስክር ክፍያ በቀን $40 ነው፡፡ ዲሲ ወስጥ ለማይኖር ምስክር ደግሞየትራንስፖርት ክፍያ መክፈል አለቦት፡፡ የፍርድ ቤት መጥሪያ ለምስክር የሚያደርሰውሰውሲያደርስ ለምስክሩ ገንዘብ መክፈል አለበት፡፡

የምስክር ክፍያ መክፈል ካልቻሉ፣ ላለመክፈል የፍርድ ቤቱን ፈቃድ መጠየቅ ይችላሉ፡፡ ይህን ለማድረግ ‹‹ቅድመክፍያ ሳይከፍሉ ማመልከቻ እንዲቀጥል›› ማመልከት አለቦት፡፡ ለጥያቄህ መልስ በሚሰጠዉዳኛ ፊት ቆመውዳኛውጥያቄዎን ይቀበላሉ ወይምውድቅ ያደርጋሉ። ጥያቄዎ ተቀባይነት ካገኘ የምስክር ክፍያ ሳይከፍሉ የፍርድ ቤት መጥሪያ መስጠት ይችላሉ፤ ነገር ግን ክፍያ መክፈል የለቦትምየሚለውን ትእዛዝ ቅጂ ማያያዝ ይኖርቦታል፡፡